# የሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ!

ሀገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ የምትገኝበትን አስከፊና በረጂም ታሪኳ ውስጥ ታይቶም ተሰም
ቶም የማይታወቅ የቡድን አምባገነናዊ አገዛዝ ተጠናክሮ ጭራሽ በንቀት ሕዝብን በረሀብ
መቅጣት ደረጃ ላይ ተደርሷል። በመሆኑም፥

- ሕዝባችን በግንቦት 15 - 1997 (ሜይ 7/2005) በምርጫ ካርድ በምመርጣቸው መሪ
ዎቹ ብቻ ነው የምተዳደረው ብሎ በቁርጠኝነት የወሰነበት እለት መሆኑን ለመዘከር፤

- የ1997ቱ ምርጫ እንደተጭበረበረ ቀርቶ አምባገነናዊው ቡድን ስልጣኑን የሙጥኝ
ብሎ ተመራጮቹን ማሰሩ፣ ማንገላታቱና ማዋከቡ አንሶት ዛሬም ብቻውን የተወዳደረበት
«ምርጫ» ብሎ ማደናገሩና ማጭበርበሩን መቀጠሉ፣ አጥብቀን የምንቃወም መሆናችንን
ለማሳየት

- አልመረጠኝም፣ አይደግፈኝም ብሎ የፈረጀውን ከተሜ ለመገመት በሚያዳግት
የኑሮ ውድነት በመቅጣትና በማፈናቀል ላይ መሆኑን፣

- ኢትዮጵያን ለማፈራረስና ሕዝቦቿን ለማጨራረስ የተለመው እኩይ ዓላማው በሕዝባ
ችን አስተዋይነትና በእግዚአብሄር ቸርነት አልሳካ ቢለው የኢትዮጵያን መሬት ቆርሶ ለ
ጎረቤት አገር በመስጠት ላይ በመሆኑ፤ አያገባው ገብቶ የጎረቤት ሀገር በመውረር በአካ
ባቢው ሕዝቦች ዘንድ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደጠላት እንዲቆጠር ሆን ብሎ የሚሰራው
ደባ ባስቸኳይ እንዲቆም፤

- በሕገ መንግሥቱ ላይ የተደነገጉት የመናገር የመጻፍና የሰላማዊ ሰልፍ መብቶች መታ
ቀባቸውን በመቃወም፣ አሁንም እንደትናንቱ በነጻ ሜዲያው ላይ የጀመረውን የማጥፋት
ዘመቻ በአስቸኳይ እንዲያቆም፣

- በኢትዮጵያዊነታቸውና ለሕዝብ አንድነት የሚታገሉ ንጹሃን ዜጎች፣ አርቲስቶች፣
ጋዜጠኞች፤ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችና ለአብነት በቅርቡ እንደ «ቴዲ አፍሮ» ያሉ
ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጆች ላይ በሰበብ በአስባቡ ማሰሩን በትራፊክ አደጋ ተጠርጣሪን
በጨለማ ቤት ውስጥ ከሌሎች እስረኞች እንዲገለል አድርጎ በጽኑ እስር ማሰቃየት ከ
ምንና ለምን እንደመነጨ ለዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ አጥብቆ ለማጋለጥ፣ ከዚህ አይነቱ
የለየለት አምባ ገነንነት እንዲቆጠብ ጫና እንዲደረግበት፤

- ይህ በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን አስከፊ ሁኔታ በውል በመረዳት በስዊዘርላንድ የስደተኝነ
ት መብት ተነፍገው በመንገላታት ላይ ለሚገኙ ወገኖቻችንና በየሀገሩ ተበታትነው በስቃይ
ና በእስር ቤቶች ላይ ላሉ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን፤ ለምሳሌም በሱዳን፣ ግብጽ፣ሊቢ
ያና እስራኤል ታስረው የሚገኙበትን ሁኔታ ለሚመለከተው ክፍል ተማጽኖ ለማቅረብበ
ሜይ 16 ቀን 2008 ጄኔቫ በተባበሩት መንግስታት ጽ/ቤት አደባባይ (Palais des Nations)
ከቀኑ 13 ሰኣት ጀምሮ የሰላማዊ ሰልፍ ላይ ያልሰሙትን አስምታችሁ እንድትገኙ
በስዊዘርላንድ የምንገኝ የተቃዋሚ ድርጅቶች የድጋፍ ሰጪ አካላትና የኢትዮጵያ ማህበር
በመተባበር ጥሪ እናቀርባለን።

ሰላማዊ ሰልፉ ከሜይ 15 ጀምሮ እስከ ሜይ 18 ባሉት ቀናት በዓለም ዙርያ የምንኖር
ኢትዮጵያውያን ከምናደርጋቸው ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች አንዱ አካል ነው።

እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይጠብቅ!!

---

ተጨማሪ መረጃ፣ በሚቀጥሉት የስልክ ቁጥሮች ማግኘት ይቻላል።

**መስፍን** 076 542 3155 - **ዘካርያስ** 076 248 72 92 - **ዉሂብ** 079 479 89 04 - **አንዱ ዓለም** 076 248 88
01 - **ወ/.ሮ መሰረት** 079 776 87 73 -**መሂር** 076 495 99 64 **ሰለሞን** 078 611 90 37